# ያላግባብ በተከፈተ አፍ ውስጥ ባዶ ጭንቅላት ይታያል

**ከእስክ ነጻነት**
eske.netsanet@hotmail.com

አቶ ቡልቻ ደመቅሳ እ ኤ አ May 6 2009, በVOA ወያኔ መንግስቴን ሊገለብጡ ነው፣ አይ ቆይ በባለ ስልጣኖቼ ላይ ግድያ ሊፈጽሙ ነው ብሎ ግንቦት ሰባትን እንደ ዋቤ አድርጎ የአማራ ብሄር ወታደሮችንና ሰላማዊ ዜጎችን እያሰረ ያለበትን ሁኔታ ተጠይቀው በገለልተኛ አካል እስካልተጣራ ድረስ አላምንም ብለው በሰጡት አስተያየት ላይ መንግስት ያለውን ምን ይላል ተብለው የተጠየቁት ሚኒስትር ደኤታ አይተ ኤርሚያስ ለዚህ አስተያየት የለኝም፣ ይህን አስተያየት ከሰጡ ወንጀለኛ ናቸው ነበር አጭር መልሳቸው:

ሚንስትር ድኤታ ናቸው ህገ ወያኔን አያውቁትም ማለት አይቻልም: አንድ ሰው ወንጀለኛ ለመባል ህገ ወያኔው አንቀጽ 20፣ ንኡስ አንቀጽ 3 እንደዚህ ያስቀምጠዋል:

***“Article 20 Rights of the Accused.***

***3. Everyone charged with an offence shall be presumed innocent until proved guilty by a court of law and not to be compelled to testify against himself. “***

እንኳን የፓርላማ አባል ቀርቶ በወንጀል የተከሰሰ ሰው እንኳ በህግ እስኪረጋገጥ ድረስ ወንጀለኛ አይደለም ይላል: ለክቡር አይተ ኤርምያስ ግን ይህ አይሰራም: የወያኔን ቃል፣ ተግባር አሜን ብሎ ካልተቀበለ ወንጀለኛ ነው: በቃ::

ሌላው የህገ ወያኔ ሐሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ብሎ ባስቀመጠው አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ አንድና ሁለት እንደዚህ ያስቀምጡታል:

***“Article 29 Right to Hold Opinions, Thoughts and Free Expressions***

***1. Everyone shall have the right to hold opinions without any interference.***

***2. Everyone shall have the right to freedom of expression without interference. This right shall include freedom to seek, receive and impart information and ideas of all kinds, regardless of frontiers, either orally, in writing or in print, in the form of art, or through other media of his choice. “***

እንኳን የፓርላማ አባል ቀርቶ ማንኛውም ዜጋ ኃሳቡን በነጻ መግለጽ እንደሚችል: ለማጭበርበሪያም ቢሆን ህገ ወያኔ አስቀምጦታል:

**አይተ ኤርምያስ ግን ብዙ አድምጭ ባለው ብዙሐን መገናኛ አፋቸውን ሞልተው፣ ትንሽ ኃፍረት፣ ኃላፊነት ሳይሰማቸው በማን አለብኝነት ወንጀለኛ ናቸው ብለው አፋቸውን ሲከፍቱ ያሳዩት ባዶ ጭንቅላታቸውን ነበር:**

**ህግና ስርዓት ያለበት ሐገር ቢሆን ኖሮ በአስቸኳይ ይቅርታ እንዲጠይቁን ከስልጣናቸው እንዲነሱ ይደረግ ነበር: ነገር ግን ያለንበት መንግስትም፣ ህግም፣ ህግ አስከባሪም፣ ዳኛም፣ አቃቤ ህግም ወያኔ ስለሆነ ለጊዜው ምንም ማድረግ አይቻልም:**

**በጣም የሚገርመው ግን** 18 **ዓመት ሙሉ እንደዚህ ባሉ ቀፎ ጭንቅላት ስንሰቃይ መኖራችን ነው**::

Better late than Never

**አሁንም ይደርሳል**

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ**::